# ትምህርት ቤት መሰረት ያደረገ የ Medicaid/FAMIS ፕሮግራም በተደጋጋሚ የሚነሱ ጥያቄዎች፡-

የአካል ጉዳት ላላቸው ግለሰቦች የትምህርት ሕግ (Individuals with Disabilities Education Act) (IDEA)፤ ለአንዳንድ የግል ትምህርት መርሃ ግብር (IEP) አገልግሎቶች በMedicaid እንዲሸፈን እንዲሁም የArlington የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (APS)፤ የቨርጂኒያ የሕክምና እርዳታ አገልግሎቶች መምሪያ (DMAS) ክፍያ እንዲያስከፍል ይፈቅዳል። እነዚህ አገልግሎቶች የአካል ቴራፒ፣ የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ ቴራፒ፣ የንግግር / የቋንቋ ሕክምና አገልግሎቶች፣ የሰለጠነ የነርስ አገልግሎቶች፣ የግል እንክብካቤ እርዳታዎች፣ ልዩ የመጓጓዣ, አንዳንድ ግምገማዎችን ያካትታል። ሜዲኬድን ለማስከፈል፤ APS የወላጅ ስምምነት ማግኘት አለበት።

ከዚህ በታች ያለውን ትምህርት ቤት መሰረት ያደረገ የ Medicaid ፕሮግራም በተመለከተ በተደጋጋሚ የሚነሱ ጥያቄዎች ዝርዝር ነው፡-

1. **ለምንድን ነው ትምህርት ቤቶች የ Medicaid / FAMIS የይገባኛል ክፍያ ለማስከፈል የወላጅ ስምምነት የሚያስፈልጋቸው?**
   APS፤ የአካል ጉዳት ስላለበት ተማሪ መረጃ አሳልፎ ከመስጠቱ በፊት የወላጅ ስምምነት እንዲኖረው በቤተሰብ የትምህርት መብት እና የምስጢራዊነት ሕግ (FERPA) ይገደዳል። ይህም ለ Medicaid (DMAS) ኤጀንሲ መረጃ መስጠትንም ያካትታል።

2. **በልጄ የ IEP ውስጥ ለተገለጹት አገልግሎቶች Medicaid / FAMISን ለማስከፈል APS ምን ያህል ጊዜ የእኔን ስምምነት ማግኘት ያስፈልገዋል?**
   የወላጅ ስምምነት የሚያስፈልገው አንድ ጊዜ ብቻ ነው። ልጅዎ በAPS ተመዝግቦ እስካለ ድረስ፤ ልጅዎ በየአንዳንዱ IEP ክፍያ የሚከፈልባቸው አገልግሎቶች መቀበል እስኪያቆም ወይም እርስዎ ስምምነትዎን እስኪሽሩ ስምምነቱ ተቀባይነት አለው።

3. **ልጄ ለ Medicaid ብቁ አይደለም። ይህም ሆኖ ሳለ ስምምነቱን መፈረም ያስፈልገኛልን?**
   አዎ ልጅዎ ለMedicaid ብቁ ከሆነ፤ የእርስዎ ስምምነት ፋይል ይደረጋል ።

4. **ስምምነቴን ከሰጠሁ በኋላ ሐሳቤን ብለውጥ ምን ይሆናል?**
   የወላጅ ስምምነት በፍላጎት የሚሰጥ ስለሆነ በማንኛውም ጊዜ መሻር ይችላሉ። ስምምነት ሰጥተው ሲያበቁ በኋላ ግን ቢሽሩ፤ የተሻረ ተመላሽ አይሆንም፤ እንዲሁም ስምምነቱ እያለ ለተደረጉ አገልግሎቶች የ Medicaid (DMAS) ኤጀንሲ እንዲከፍል ይደረጋል። የስምምነት ውሳኔዎን መለወጥ ከፈለጉ፤ እባክዎን በስልክ ቁጥር (703)228-6065 ለ Medicaid አስተባባሪ ይደውሉ።

5. **ስምምነት ባልሰጥ ምን ይሆናል?**
   የልጅዎን የትምህርት ፕሮግራም በIEP እንደተገለጸው በትምህርት ፍላጎቶቹ/ቿ ላይ የተመሠረተ ነው። የMedicaid/FAMIS ስምምነት ሁኔታ ምንም ይሁን የእርስዎ የስምምነት ውሳኔ በእርሱ/ሷ አገልግሎት ላይ ምንም ተፅዕኖ አይኖረውም። ይሁን እንጂ፣ ስምምነት መከልከል የአካል ጉዳት ላለባቸው ተማሪዎች ትምህርት የሚጠቅም ገንዘብ ዲስትሪክቱ የማግኘት ችሎታው ላይ ተጽዕኖ ያሳድራል።

6. **ልጄ የ Medicaid/FAMIS ጥቅሞችን ባያገኝ ምን ይሆናል?**

APS ለአገልግሎቶች ማስከፈል የሚችለው አንድ ልጅ የ Medicaid / FAMIS ጥቅሞች ለመቀበል ተለይቶ ከሆነ ብቻ ነው። የMedicaid/FAMIS ጥቅሞች ማጣት፤ ልጅዎ በትምህርት ቤት የሚያገኛቸው አገልግሎቶች ላይ ተጽዕኖ አይኖረውም።

7. **በMedicaid/FAMIS ክፍያ ምክንያት የግል ሚስጥሬ ላይ ችግር ይፈጥር ይሆን?**
   APS ሐኪም በሚያደርገው መልኩ Medicaidን ያስከፍላል። APS የእርስዎን የጤና መረጃ ምስጢራዊነት ጠብቀን ለማቆየት የሚያስገድዱንን ጥብቅ የፌደራል እና የስቴት ህጎች ይከተላል። የልጅዎን መረጃ ማግኘት የሚችሉት በቀጥታ ተሳታፊ ለሆኑት ብቻ የተወሰነ ነው።

8. **የግል ኢንሹራንሴ ተጽዕኖ ይደርስበታል ወይ?**
   አይ። APS፤ ከ IEP ጋር ለተያያዙ አገልግሎቶች የግል ኢንሹራንስዎን ክፍያ አይጠይቅም። የስምምነቱን ቅጽ መፈረም የግል ኢንሹራንስዎን ጥቅሞችም ሆነ ሌላ እርስዎ ወይም ቤተሰብዎ የምታገኙት የMedicaid/FAMIS አገልግሎት እንደማይቀንስ ማወቅዎ አስፈላጊ ነው።

9. **የትምህርት ቤቱ አከፋፈል ለግል አገልግሎቶች ለተፈቀደልኝ ከፍተኛ የመታያ ጊዜ መጠኖች አይቆጠርም ወይ?**
   አይ። APS ክፍያ እንዲወራረድለት ሲፈልግ፤ የግል አገልግሎቶች በሚሰጡበት እነኚህ የተፈቀዱ ከፍተኛ የመታያ ጊዜያት መጠን ላይ ተጽዕኖ አይኖረውም። ከውጭ ባለሙያ የሚቀበለው የMedicaid/FAMIS አገልግሎቶች፤ ከትምህርት ቤቱ ከሚቀበለው ተለይቶ ነው የሚፈቀደው።

10. **ለምንድን ነው የMedicaid ሂሳብ በትምህርት ቤቱ በኩል የሚሰጠው?**
    የሂሳብ አከፋፈሉ ለተማሪዎች የተሰጡትን የአገልግሎት ዋጋዎች ለማወራረድ ስለሚረዳ።

**ማንኛውም ጥያቄ ካልዎት እባክዎን የ Medicaid አስተባባሪ የሆኑትን Catina Claytor ያነጋግሩ።**

1426 N. Quincy Street
Arlington, VA 22207
(703) 228-6065
catina.claytor@apsva.us